በገቢ እቃዎች የሚጣሉ የቀረጥና ታክስ አይነቶች

ከታክስ ነፃ እንዲሆኑ በህግ ከተፈቀደላቸው በስተቀር፣ ወደ ሃገራችን በሚገቡ እቃዎች ላይ አምስት የታክስ አይነቶች ይጣላሉ። እነዚህ የታክስ ዓይነቶች በገቢ እቃው ላይ የሚጣሉበት እና የሚሰሉበት ስነ ስርዓት በቅደም ተከተል ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት በገቢ እቃው ላይ የሚጣሉት አምስቱ የታክስ አይነቶች የጉምሩክ ቀረጥ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ሱር ታክስ እና ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ የሚሉት ናቸው።

እነዚህ ታክሶች ለመሰረተ ልማት ግንባታ እና ለሌሎችም በመንግስት ለሚታቀዱ የተለያዩ ስራዎች ማስኬጃ የሚደለደለውን ገንዘብ ለማመንጨት በመሳሪያነት ያገለግላሉ። ለምሳሌ በ2002 በጀት ዓመት ታክስና ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች 35.6 ቢሊዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን ከዚህ ገቢ ውስጥ 18 ቢሊዮን ብር ወይም 51.76 በመቶ የሚሆነው ገቢ የተሰበሰበው በገቢ እቃዎች ላይ ከተጣሉት የታክስ አይነቶች ነው። ቀሪው 17.6 ቢሊዮን ብር የተሰበሰበው ከሀገር ውስጥ ገቢ፣ ከሎተሪ ሽያጭ እና ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች ነው። በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሠረት በማድረግ ከእነዚህ ታክሶች የሚገኘውን ገቢ የሚሰበስበው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

በዚህ ፅሑፍ በገቢ እቃዎች ላይ የሚጣሉ የታክስ አይነቶችን እና የስሌት ቀመራቸውን ለማብራራት ተሞክሯል።

1. የጉምሩክ ቀረጥና መጣኔው

በገቢ እቃዎች ላይ ከሚጣሉት ታክሶች የመጀመሪያውንና የቀደምትነቱን ስፍራ የሚይዘው የጉምሩክ ቀረጥ /customs duty/ ነው። የጉምሩክ ቀረጥ በገቢ ወይም በወጪ እቃዎች ላይ የሚጣል የታክስ ዓይነት ነው።

የጉምሩክ ቀረጥ የገቢ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን የሚያገለግል ሲሆን በ2002 በጀት አመት መንግስት ከጉምሩክ ቀረጥ ብቻ 5.8 ቢሊዮን ብር ሰብስቧል። በበጀት አመቱ ከገቢ ዕቃዎች ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ፣ የጉምሩክ ቀረጥ አስተዋጽኦ 31.6 በመቶ እንደሆነ ታውቋል።

በአንድ የገቢ እቃ ላይ የሚጣለው የጉምሩክ ቀረጥ የሚሰላው በእቃው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ /Duty Paying Value/ ላይ ተመርኩዞ ነው። የእቃው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ እቃውን ወደ

ሃገር ለማስገባት አስመጪው የፈፀማቸው ልዩ ልዩ ክፍያዎች ድምር ውጤት ነው። ይህ ድምር ወደ ሃገር የሚገባውን እቃ ለመግዛት አስመጪው የከፈለውን ገንዘብ /የእቃውን ዋጋ/፣ ለኢንሹራንስ የተከፈለን ገንዘብ /የመድን አረቦን/ እና የማንጓጓዣ ወጪን /Freight/ ያካትታል፡ የማንጓጓዣ ወጪ ዕቃውን እስከ ጂቡቲ ወደብ እንዲሁም ከወደቡ እስከ መጀመሪያው የሀገራችን መግቢያ ድንበር(ጋላፊ) ድረስ ለማንጓዝ፡ የተከፈለን ገንዘብ ይጨምራል። በእቃው አስመጪ የተፈፀሙ እነዚህ ክፍያዎች ተደምረው የተገኘው ውጤት በእቃው የቀረጥ ማስከፈያ መጣኔ ሲባዛ ተከፋዩን የጉምሩክ ቀረጥ እናገኛለን።

ተከፋዩን የጉምሩክ ቀረጥ ለማስላት የሚያገለግሉት የቀረጥ መጣኔዎች ስድስት ናቸው። እነዚህ መጣኔዎች 0%፣ 5%፣ 10%፣ 20%፣ 30%፣ እና 35%፣ ናቸው። ከዚህ የምንገነዘበው በገቢ እቃው ላይ የሚጣለው አነስተኛው የቀረጥ መጣኔ 0፣ ሲሆን ከፍተኛው 35 በመቶ መሆኑን ነው። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊያጭርብን ይችላል። እሱም፣ አንደኛው ገቢ እቃ ከቀረጥ ነጻ ወይም በዜሮ የቀረጥ መጣኔ ወደ ሀገራችን ሲገባ ሌላው ለምን በከፍተኛ የቀረጥ መጣኔ ወይም በ35 በመቶ ይቀረጣል የሚል ነው። ይህ የሚሆንበት አይነተኛ ምክንያት ገቢ እቃው ከሚሰጠው ጠቀሜታ ወይም አገልግሎት ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው። ገቢ እቃው ለምርት ስራ ጉዳይ የሚውል፣ ወደ ውጭ ሃገር የሚላኩ እቃዎችን ለማምረት በግብዓትነት የሚያገለግል፣ እና ለህዝብ አገልግሎት የሚውል ከሆነ በዜሮ የቀረጥ መጣኔ ወይም በአነስተኛ የቀረጥ መጣኔ ወደ ሀገራችን እንዲገባ ይፈቀድለታል። በዚህ መሠረት ለግብርና ምርት በግብአትነት የሚያገለግል የአፈር ማዳበሪያ ወይም የፋብሪካ ጥሬ እቃዎች፣ የምርት መገልገያ መሳሪያዎች እና የህዝብና ደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች_ለምሳሌ አውቶቡስ ወዘተ የሚሉት በዜሮ ወይም እስከ 10 በመቶ በሚደርስ አነስተኛ የቀረጥ መጣኔ ወደ ሀገራችን እንዲገቡ ከሚፈቀድላቸው እቃዎች መካከል ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በቀጥታ ለምርት ስራ ጉዳይ ከሚውሉት ከጥሬ እቃዎች እና ከኢንቨስትመንት እቃዎች ቀጥሎ ወደ ሃገር እንዲገቡ የሚበረታቱት በከፊል የተዘጋጁ እቃዎች /Semi finished goods/ ናቸው። የእነዚህ እቃዎች የምርት ሂደት በከፊል በውጭ ሃገር የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪው የምርት ሂደታቸው ተጠናቆ ለገበያ የሚቀርቡት ወደ ሃገራችን ከገቡ በኋላ ነው። እነዚህ እቃዎች ወደ ሃገር ሲገቡ የ10 ወይም የ20 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ይጣልባቸዋል።

በተቃራኒው ለልማት ስራ ጉዳይ ሳይሆን የግለሰቦችን ወይም የህብረተሰቡን የሸቀጥ ፍላጐት ለማሟላት ወደ ሃገራችን የሚገቡ የፍጆታ እቃዎች ከፍተኛ የጉምሩክ ቀረጥ ይጣልባቸዋል።

ለምሳሌ የግለሰብን ምቾት ለመጠበቅ የሚያገለግል አንድ የቤት መኪና 35 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ የሚጣልበት ሲሆን በሌላ በኩል ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውል አንድ አንቡላንስ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር እንዲገባ ይፈቀድለታል። ከዚህ ምሳሌ የምንገነዘበው ለሀገር እድገትና ልማት እንዲሁም ለህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ መሻሻል ፋይዳ ያላቸው ዕቃዎች ወደ ሀገር እንዲገቡ የሚበረታቱ መሆናቸውን ነው። ይህ ማበረታቻ ለምርት እና ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚውሉ እቃዎችን ከቀረጥ ነጻ ወይም አነስተኛ ቀረጥ ተከፍሎባቸው እንዲገቡ የሚያደርግ ሲሆን በዚህ መሠረት ከ1996 እስከ 2002 በጀት ዓመት የተተወውን ቀረጥና ታክስ ከተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ጋር በማነፃፀር የሚያሳይ ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

	1996	1997	1998	1999	2000	2001	2002
በገቢ እቃዎች ላይ ከተጣለ ቀረጥና ታክስ የተሰበሰበ ገቢ በቢሊዮን ብር	5.3 ቢለዮን	5.7	6.6	7.7	11.2	12.2	18.1
በቀረጥ ነፃ የገቡ እቃዎች በቢሊዮን ብር	6.07 ቢለዮን ብር	5.3	4	4.9	9.7	15	19.9

በሠንጠረዡ ለማሳየት እንደተሞከረው በ2002 ዓ.ም. ብቻ 19.9 ቢሊዩን ብር ገቢ ሊያስገኙ ይችሉ የነበሩ እቃዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ተደርጓል። በዚህ በጀት ዓመት በቀረጥ ነፃ የገባው እቃ መጠን ቀረጥ ተከፍሎበት ከገባው ዕቃ በ1.8 ቢሊዮን ብር ብልጫ አሳይቷል።

በቀረጥ ነጻ ዕቃዎች እንዲገቡ ከመፍቀድ በተጨማሪ የንግዱን ህብረተሰብ ለማበረታታት መንግስት የጉምሩክ ቀረጥ መጣኔን ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ በተለያየ ጊዜ ወስዷል። ለምሳሌ በተሻሻለው የጉምሩክ ታሪፍ ቅፅ 1/1996 እትም መሠረት ከፍተኛው የጉምሩክ ቀረጥ መጣኔ 60 በመቶ የነበረ ቢሆንም በ1994 እና በ1996 በተወሰደው የማሻሻያ ርምጃ ይህ መጣኔ ወደ 40 በመቶ እና ወደ 35 በመቶ ቀንሷል። ለወደፊቱም የመንግስት አላማ የጉምሩክ ቀረጥን ማስወገድ ወይም የንግድ እቃዎች በዜሮ መጣኔ ወደ ሃገር የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

1.1. ልዩ የጉምሩክ ታሪፍ (Preferential tariff)

ሀገራችን የምስራቅና እና ደቡብ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA) አባል ሃገር ነች። በመሆኑም ከአባል ሃገራት ጋር የምታደርገውን የንግድ ልውውጥ የሚያበረታታና የሚደግፍ የተለየ ታሪፍ ትጠቀማለች። በኮሜሳ አባል ሃገራት ተመርተው ወደ ሃገራችን የሚገቡ እቃዎች የሚያስተናግዱበት የተለዩ ታሪፍ እና የኮሜሳ አባል ካልሆኑ ሃገራት ተመርተው ወደ ሃገራችን በሚገቡ እቃዎች ላይ የሚጣለውን ታሪፍ የሚያመላክት ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ተ.ቁ	የኮሜሳ አባል ያልሆኑ ሀገራት የሚስተናገዱበት የጉመሩክ ታሪፍ መጣኔ በመቶኛ	የኮሜሳ አባል ሀገራት የሚስተናገዱበት ልዩ የጉመሩክ ታሪፍ መጣኔ በመቶኛ
1	5	4.5
2	10	9
3	20	18
4	30	27
5	35	31.5

1.2 የወጪ ንግድ ታክስ

ወደ ውጭ ሃገር ከሚላኩ ከተወሰኑ የቆዳና ሌጦ ምርቶች በስተቀር በሌሎች የወጪ ንግድ እቃዎች ላይ የሚጣል የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ የለም። በዓለም ገበያ የሚሸጡበትን ዋጋ ተወዳዳሪ በማድረግ የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍ ለማድረግ ሲባል ነው የወጪ ንግድ እቃዎችን ከታክስ እና ቀረጥ ነጻ ማድረግ ያስፈለገው። ይሁን እንጂ መንግስት ለዓለም ገበያ በሚቀርቡ በተወሰኑ የቆዳና ሌጦ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ ላይ የ150% ታክስ ይጥላል። ይህ ታክስ ስራ ላይ የዋለው በመመሪያ ቁጥር 25/2001 ሲሆን መመሪያውን ያወጣው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ነው። ይህ መመሪያ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ቆዳና ሌጦ በበቂ መጠን ተጨማሪ ዕሴት የታከለበት እንዲሆን ለማስቻል በክፊል ተዘጋጂቶ ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ቆዳና ሌጦ ታክስ እንዲጣል መደረጉን

ጠቁሟል::ይህ ታክስ ከሚጣልባቸው የቆዳና ሌጦ ውጤቶች መካከል ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ፣ ፒክል የበግ ሌጦ፣ ዌት ብሉ የበግ ሌጦ እና ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ የሚሉት ይገኙበታል::

2.. ኤክሳይዝ ታክስ ምንድን ነው?

ይህ ታክስ የቅንጦት እና መሠረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገቢያ ፍላጐታቸው በማይቀንስ ዕቃች ላይ፣ እንዲሁም የህብረተሰቡን ጤንነት የሚጐዱ እና ማህበራዊ ችግር የሚያስከትሉ ዕቃችን አጠቃቀም ለመቀነስ ሲባል የተጣለ ነው:: ታክሱ የገቢ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ጭምር ያገለግላል:: በመሆኑም፣ ባለሥልጣኑ በገቢ ዕቃዎች ላይ ከተጣለው **ኤክሳይዝ ታክስ** በ2002 በጀት አመት ወደ 2 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገቢ ሰብስቧል:: ባለሥልጣኑ በ19 ምድብ ከተደለደሉ የተለያዩ ዕቃዎች ነው ይህን ገቢ የሰበሰበው::

2.1. ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የትኞቹ ናቸው? የማስከፈያ መጣኔዎችስ?

የኤክሳይዝ ታክስ ምንጭ የሆኑት ዕቃች ዝርዝር ቀጥሎ በሚቀርበው ሠንጠረዥ የተመለከተ ሲሆን ከእነዚህ ዕቃች የሚገኘውን ታክስ ለመሰብሰብ ባለሥልጣኑ የሚገለገልበት አነስተኛው መጣኔ ወይም የማስከፈያ ልክ /rate/ **በመቶኛ 10** ሲሆን ከፍተኛው **በመቶኛ 100** ነው:: የኤክሳይዝ ታክስን መጣኔች ከአስር መመደብ ይቻላል:: እነሱም 10፣20፣30፣33፣40፣50፣60፣75፣80 እና 100 ናቸው:: እነዚህ መጣኔዎች ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ለማስላት ያገለግላሉ::

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት	የኤክሳይዝ ታክስ በመቶኛ%
1	ማናቸውም ዓይነት ስኳር /በአንኳር መልክ/ ሞላሰሰን ሳይጨምር---------- 33	
2	መጠጦች 2.1 ማናቸውም ለስላሳ መጠጦች /ከፍሬ ጭማቂዎችና እነዚህን ከመሳሰሉ በስተቀር –30	

	2.2 በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ለስላሳ መጠጦች ——— 30
	2.3 በፋብሪካ የሚመረት የታሸገ ውሃ ---------- 20
	2.4 ማናቸውም አልኮል ያላቸው መጠጦች
	2.4.1 ማናቸውም ቢራና ስታውት ---------- 50
	2.4.2 ማናቸውም የወይን ጠጅ መጠጦች ----- 50
	2.4.3 ዊስኪ ---------- 50
3	2.5.4 ሌሎች አልኮል ያለባቸው መጠጦች ---- 100
4	ማናቸውም አይነት ንፁህ አልኮል ---------- 75
	ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶች
	4.1 የትምባሆ ቅጠል ---------- 20
	4.2 ሲጋሬት፣ ሲጋራ፣ ሲጋሪሎስ፣
	የፒፓ ትምባሆ፣ ሱረትና ሌሎች የትምባሆ
5	ውጤቶች ---------- 75
6	ጨው ----------—--- 30
	ነዳጅ የአውሮፕላን ነዳጅ፣ ሱፐር ቤንዚን፣
	ተራ ቤንዚን፣ ፔትሮል፣ ጋዛሊን እና ሌሎች
7	የሞተር ስፕሪት ----------—---- 30
	ሽቶዎች እና ቶይለት ወተርስ ----------—--------- 100
8	በፋብሪካ ከጨርቃ ጨርቅ የተሰሩ
	ወይም የተዘጋጁ ልብሶች ----------—---- 10
	8.1 ከተፈጥሮ ሐር፣ ከናይለን፣
	ከሱፍ፣ ወይም ከማናቸውም ሌሎች
	ተመሳሳይ ነገሮች በሹራብ መልክ ቢሆን

	የተሰሩ ጨርቃ ጨርቆች ----------—---- 10 8.2 በሙሉ ሆነ በከፊል የተሰራ አመድማ፣ ነጭ ቀለም የተነከረ ወይም የታተመ፣ በማናቸውም ቁመት ወይም ወርድ የተሰራ ጨርቃ ጨርቅ ከወባ መከላከያ አጎበር እና ከአቡጀዲ በስተቀር/ እንዲሁም የብርድ ልብሶች አንሶላዎች፣

	የአልጋ ሽፋኖች፣ ፎጣዎች፣ የጠረጴዛ ልብሶች እነዚህንም የመሳሰሉ ጨርቃ ጨርቆች —-10 8.3 ከጨርቃ ጨርቅ የተሰሩ ወይም
9	የተዘጋጁ ልብሶች ----------—---------- 10
	ከወርቅ ከብርና ከሌሎች ነገሮች
10	የተሰሩ ጌጣ ጌጦች ----------—------ 20
	ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚሆኑ
11	ሳህን ማጠቢያ መኪናዎች ----------—----- 80
	ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚሆኑ
12	የልብስ ማጠቢያ መኪናዎች ----------—------ 30
13	የቪዲዩ ዴክ ---------- 40
14	የቴሌቪዥን እና የቪዲዩ ካሜራዎች ----------—---40
	ተቀባይ ቴሌቪዥን፣ ከግራማፎን ከራዲዩ፣

	ወይም ከድምፅ መቅረጫና ማሰሚና
15	ማሳሪያዎች ጋር የተጣመሩ ቢሆንም ባይሆንም -- 10
	ለመንገደኞች መጓጓዣ የሚሆኑ
	ተሸከርካሪዎች /አውቶሞቢሎች/ እስቴሽን
	ዋገን የአገልግሎት መኪናዎች ላንድሮቨሮች፣
	ጂፓች፣ ፒክአፖች፣ እ ና እነዚህን
	የመሳሰሉ ተሸከርካሪዎች በላሞተር
	ክራቫኖች ጭምር የተገጣጠሙ ወይም
	ያልተገጠሙ በመጀመሪያ ሲወጡ ሊኖራቸው
	ከሚገባው መሳሪያ ጋር
16	15.1 እስከ 1300 ሲ.ሲ ----------—---- 30
17	15.2 ከ1301 ሲ.ሲ በላይ እስከ 1800 ሲ.ሲ -----— 60
18	15.3 ከ1800 ሲ.ሲ በላይ ---------- 100
19	የወለል ምንጣፎች ---------- 30
	የአስቤስቶስና የአስቤስቶስ ውጤቶች ---------- 20
	የጠረጴዛ፣ የግድግዳና የእጅ ሰዓቶች ---------- 20
	ሻንጉሊቶችና መጫዎቻዎች ———————-- 20

2.2. ኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ በማን ላይ የተጣለ ነው?

በሠንጠረዡ በተመለከቱት ዕቃዎች ላይ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣለው ዕቃው ወደ ሀገር ሲገባ ወይም በሃገር ውስጥ ሲመረት ሲሆን ታክሱን የመክፈል ግዴታ በአስመጭው ወይም በአምራቹ ላይ የተጣለ ነው።

2.3. የኤክሳይዝ ታክስ የስሌት መሠረት ምንድን ነው?

ማንኛውም ግብር ከፋይ የሚጠበቅበት ግብር አስልቶ የማስታወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት። ወደ ሃገር ውስጥ በሚገባ ዕቃ ላይ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ለማስላት አራት ነገሮችን መደመር ያስፈልጋል። እነሱም የዕቃው ዋጋ ሲደመር የመድን አረቦን ሲደመር የማንጓጓ ወጪ ሲደመር በዕቃው ላይ የሚከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ናቸው። የእነዚህን ድምር ውጤት በማስከፈያ ልክ ስናባዛ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን እናገኛለን ማለት ነው።

በሌላ በኩል በሃገር ውስጥ በተመረቱ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለው ኤክሳይዝ ታክስ የስሌት መሠረት የዕቃው የምርት ወጪ እና የዕቃው ማስከፈያ ልክ /rate/ ናቸው ሊባል ይችላል። ለመንግስት የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላውም /የምርት ወጪውንና የማስከፈያ ልክን/rate/ በማባዛት ነው። የምርት ወጪ ሲባል ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን እቃ ለማምረት የዋሉ የጥሬ ዕቃዎችና የጉልበት ዋጋ፣ ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብዓቶች ወጪ እና ኦቨርሄድ ወጪ ማለት ሲሆን ለማምረቻ መሳሪያዎች የሚታሰበውን የዕርጅና ቅናሽ አይጨምርም።

በአገር ውስጥ በፋብሪካ በተመረቱ ከጨርቃ ጨርቅ የተሰሩ ወይም የተዘጋጁ ልብሶች እና አገር ውስጥ የተገጣጠሙ ተሽከርካሪዎች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ ማስላት ሲያስፈልግ ለእነዚህ ዕቃዎች ማምረቻ የዋሉ ግብዓቶች ወደ አገር ሲገቡ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተቀናሽ ይደረጋል።

2.4. የኤክሳይዝ ታክስ የክፍያ ጊዜ መቼ ነው?

በሠንጠረዥ የተመለከቱትን ዕቃዎች ወደ ሃገር ውስጥ ያስገባ አስመጪ ዕቃዎቹን ከጉምሩክ ክልል በሚያወጣበት ጊዜ ኤክሳይዝ ታክስ ይከፍላል። ዕቃው በሃገር ውስጥ የተመረተ ከሆነ ከተመረተበት ወር ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል በመመሪያ ቁ.18/2001 ተደንግጓል።

3. ተጨማሪ እሴት ታክስ

ተጨማሪ እሴት ታክስ በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጣሉት አምስቱ የታክስ አይነቶች መካከል አንደኛው ነው። ይህ ታክስ የሀገራችንን የታክስ ስርዓት አካል የሆነው በአዋጂ ቁጥር 285/1995 ነው። የዚህ ታክስ መጣኔ 15 በመቶ ሲሆን ታክሱ የሚከተለውን ቀመር ተከትሎ ይሰላል። በዚህ ቀመር መሰረት አስመጪው የእቃውን ዋጋ፣ የመድን አረቦን፣ የማንጓጓዣ ወጪ፣ የጉምሩክን ቀረጥ እና ኤክሳዩዝ ታክስን በአንድነት ይደምራል፤ በመቀጠል፣ የድምሩን ውጤት በ15 ከመቶ በማባዛት አስመጪው ተከፋዩን ተጨማሪ እሴት ታክስ ያገኛል ማለት ነው። ታክሱ የገቢ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ ታክስ በ2002 በጀት አመት፡፩.፭ ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል። በበጀት አመቱ ከገቢ ዕቃዎች ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዋጽኦ 34.14 በመቶ እንደሆነ ታውቋል።

መንግስት ወደ ሀገራችን በሚገቡት በማናቸውም ዕቃዎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ ሁሉ ተጨማሪ እሴት ታክስ ይጥላል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፣ የሚከተሉት ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ናቸው፣ዕቃዎቹ ከዚህ ታክስ ነጻ የተደረጉት በአዋጂ ቁጥር 285/1995 አንቀጽ 8፣አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 79/1995 *ክፍል ሁለት* /ከአንቀጽ 19 - 33/ *በተደነገገው እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር* 285/94 *አንቀጽ* 8/4/ *በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከታክሱ ነፃ ያደረጋቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ናቸው።እነዘህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዝ የተዘረዘሩ ሲሆን ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ በውጭ ሀገር ወይም በሀገር ውስጥ የተመረቱ ሊሆኑ ይችላሉ።*

ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ ዋና ዋና ዕቃዎች/አገልግሎቶች ዝርዝር		
ተ.ቁ	**የዕቃው /አገልግሎቱ ዓይነት**	**ነፃ የተደረገበት የህግ መሠረት /አዋጅ/መመሪያ/ሰርኩላር ቁጥር**
1	ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ	የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994

2	የፋይናንስ አገልግሎቶች	»	»	»	»
3	ለማንቲሞች እና ሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎቶች ከሚውሉት በስተቀር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦችን እና የዋስትና ሰነዶችን ማሰራጨት ወይም ወደ አገር ማስገባት	»	»	»	»
4	ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደ አገር ማስገባት	»	»	»	»
5	በሀይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች	»	»	»	»
6	በትምህርት ተቋማት የሚሠጡ የማስተማር አገልግሎቶች እንደዚሁም ለህፃናት ጥበቃ በማዋዕለ ህፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች	»	»	»	»
7	የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲን እና የውሃ አገልግሎቶች /በፋብሪካ ታሽጐ የሚሸጥ ውሃን አይጨምርም/	»	»	»	»
8	ከልዩ ልዩ አገልግሎት ወይም የኮሚሽን ክፍያዎች በስተቀር የፖስታ አገልግሎት ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች	»	»	»	»
9	የትራንስፖርት አገልግሎቶች	»	»	»	»
10	ማናቸውም የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመግንስት የሚፈፀም ክፍያ	»	»	»	»
11	ከ60% በላይ ሠራተኞች አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች	»	»	»	»
12	መጻህፍት	»	»	»	»

13	የምግብ እህል /ጤፍ፣ስንዴ፣በቆሎ፣ማሽላ፣ጥራጥሬ እና የመሳሰሉት/	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/635 ቀን 09/07/2000
14	ለወባ መከላከያ አጉበር ሥራ የሚውሉ የስፌት ክር ሌብል፣ማሸጊያ ፕላስቲክ እና ማዳበሪያ	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/892 ቀን 08/07/2001
15	የቆዳ ፋብሪካዎች የሚያደርጉት የፒክል፣ የቄት ብሉ እና የክረስት ምርት ግብይት	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/860 ቀን 10/02/2001
16	የወባ መከላከያ አጉበር እና አጉበሩን ለመስፋት የሚያገልግል በኬሚካል የተነከረ ጨርቅ ወደ አገር ሲገባ	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/785 ቀን 10/02/2001
17	መንግስት ከውጭ የሚያስገባው ስንዴ	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/914 ቀን 11/02/2000
18	ከፖልም የተሰራ የምግብ ዘይት	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/644 ቀን 25/07/1994
19	የዳቦ እና የወተት ሽያጭ	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/889 ቀን 09/05/1995
20	መድኃኒቶች፣ የህክምና አቅርቦቶች እና የህክምና መገልገያዎች	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/889 ቀን 09/05/1995
21	ለግብርና ምርት የሚውሉ ማዳበሪያዎች፣ ምርጥ ዘር፣ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/930 ቀን 28/06/1995
22	የጡረታ አበል ክፍያ አገልግሎት	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/961 ቀን 01/09/1995
23	የጉዞ ወኪሎች የአውሮፕላን ቲኬት በመሸጥ የሚሰጡት የገበያ አገልግሎት	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/971 ቀን 11/10/1995
24	እንጀራ	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/13 ቀን 01/25/1996
25	የመጻህፍት ህትመት	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/185 ቀን 05/09/1997
26	የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ፋብሪካዎች ለጫማ ፋብሪካዎች የሚሸጡት የተጠናቀቀ ቆዳ	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/730 ቀን 28/11/2000
27	የቡታጋዝ ምርት	ደብዳቤ ቁጥር አመ3/16/28/227 ቀን 25/12/1997

4. ሱር ታክስ

ሱር ታክስ የመንግስትን የፋይናንስ አቅም ለማጐልበት በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጣሉት የታክስ አይነቶች መካከል አንደኛው ሲሆን በአራተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከሱር ታክስ የሚገኘው ገቢ የዋጋ ንረት የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለማርገብ ስራ ጉዳይ የሚውል ነው። መንግስት በከተማ ለሚኖሩ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሸማቾች የተለያዩ የምግብ ጥራጥሬዎችን በዝቅተኛ ዋጋ ያቀርባል። ለዚህ ስራ ማስኬጃ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት መንግስት ከሚያዝያ ወር 1999 ጀምሮ በገቢ ዕቃዎች ላይ ሱር ታክስ ጥሏል። ታክሱ የኑሮ ውድነት እንዳያስከትልና ለኢንቨስትመንት እቃዎች ዋጋ መናር ምክንያት እንዳይሆን መንግስት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጓል። የሱር ታክስ የስሌት መሠረት እቃው የተገዛበት ዋጋ፣ ኢንሹራስ /የአረበን ዋስትና/ ለማጓጓዣ የተከፈለው ዋጋ፣ የጉምሩክ ቀረጥ ኤክሳይዝ ታክስ እና ቫት ድምር ውጤት ነው። ይህ ድምር በ10 ከመቶ ሲባዛ የምናገኘው ተከፋዩን ሱር ታክስ ይሆናል።*በ2002 በጀት አመት መንግስት ለሱር ታክስ ብቻ 3.4 ቢሊዮን ብር ሰብስቧል። በበጀት አመቱ ከገቢ ዕቃዎች ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ፣ የሱር ታክስ አስተዋጽኦ 18.8 በመቶ እንደሆነ ታውቋል።*

ይሁን እንጂ የሚከተሉት ገቢ እቃዎችና አልግሎቶች ከሱር ታክስ ክፍያ ነፃ ናቸው። እነሱም የመሬት ማዳበሪያ፣ ነዳጂ እና የብረታ ብረት ቅባቶች (ሉብሪካንትስ)፣ የህዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎችም ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች፤ አውሮፕላኖች፣ የአየር መንኮራኩሮች፣ የጠፈር መንኮራኩሮች፣ እና የነዚህ ክፍሎች፤ የካፒታል (የኢንቨስትመንት) እቃዎች መድሀኒቶች ጥሬ እቃዎች እና ሌሎች በህግ ከታክስ ነፃ የተደረጉ *ዕቃዎች* ለምሳሌ *በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 1ኛ መደብ መሰረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የተደረጉት ዕቃዎች፣ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 2ኛ መደብ ሀ መሰረት በልዩ መብት ከቀረጥ ነጻ የሆኑ እንዲሁም በታሪፍ ደንቡ 2ኛ መደብ ለ መሰረት ከማናቸውም ቀረጥ ነጻ የሆኑ ዕቃዎች* ናቸው። የተለያዩ መድሃኒቶች፣ *በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 1ኛ መደብ ምዕራፍ 28 እና 29 ላይ የተዘረዘሩት እቃዎች፤ሌሎች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ከሱር ታክስ ነጻ የተደረጉ ዕቃዎች ናቸው*

5. *በገቢ እቃ ከሚጣለው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ግብር /Withholding tax on income from the imported item/)*

የንግድ ትርፍ ግብር በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጣሉት የታክስ ዓይነቶች መካከል አምስተኛውና የመጨረሻው ሲሆን ይህ ታክስ የሚተዳደረው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና አዋጁን

ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 78/1994 መሰረት ነው። በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 መሰረት ዕቃዎች ወደ ሀገር ሲገቡ የንግድ ትርፍ ግብር እንደሚጣልባቸው ተደንግጓል። በገቢ ዕቃው ላይ የሚጣለው የንግድ ትርፍ ግብር የሚሰላው የዕቃውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በ3 በመቶ በማባዛት ነው። በ2002 በጀት አመት መንግስት ከዚህ ግብር 795.8 ሚሊዮን ብር ሰብስቧል።

ይህ የንግድ ትርፍ ግብር ዕቃው በገባበት አመት መጨረሻ የሚከፈል ቢሆንም ግብሩ እቃው በሚገባበት ጊዜ አስቀድሞ እንዲከፈል ይደረጋል። ይህ የሚሆነው ያለ ምክንያት አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ አስመጪዎች በዓመቱ መጨረሻ የሚጠበቅባቸውን ግብር በመክፈል ግዴታቸውን የሚወጡ ቢሆንም አንዳንዶች ግን ግዴታቸውን ሳይወጡ የሚሰወሩበት ሁኔታ ያጋጥማል። ይህ ዓይነቱ ህገ ወጥ ድርጊት በሀገር ዕድገትና ልማት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አፍራሽ ተፅዕኖ ለመከላከል መንግሥት ውጤታማ የግብር አሰባሰብ ዘዴ ይጠቀማል። ዘዴው ትርፍ የሚያስገኙ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ የንግድ ትርፍ ግብር እንዲከፈልባቸው የሚያደርግ ነው። የመንግስትን ወቅታዊ የገንዘብ እጥረት በማቃለል ረገድም ዘዴው ጠቀሜታ እንዳለው ይነገርለታል።

አስመጪው አስቀድሞ የከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር በአመቱ መጨረሻ ከሚከፈለው የንግድ ትርፍ የግብር መጠን ላይ ይታሰባል። አስመጪው ዕቃዎችን ወደ ሀገር በሚያስገባበት ጊዜ አስቀድሞ የከፈለው ግብር አንሶ በአመቱ መጨረሻ ሊከፈል የሚገባው የግብር መጠን በልጦ ከተገኘ አስመጪው ልዩነቱን እንዲከፍል ይደረጋል። በተቃራኒው አስመጪው በየጊዜው የከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር በልጦ በዓመቱ መጨረሻ በአስመጪው ሊከፈል የሚገባው የንግድ ትርፍ ከአነሰ በትርፍ የተከፈለውን ገንዘብ ባለሥልጣኑ ለአስመጪው በ90 ቀናት ውስጥ ተመላሽ ያደርጋል። ባለሥልጣኑ በትርፍነት የተከፈለን ገንዘብ ለአስመጪው ተመላሽ ከማድረጉ በፊት አስመጪው ሌላ ግብርና ቀረጥ የማይፈለግበት መሆኑን ያረጋግጣል። ከአስመጪው የሚፈለግ ግብርና ቀረጥ ካለ ባለሥልጣኑ ተፈላጊውን ተከፋይ ግብር በተመላሹ ገንዘብ እንዲካካስ ካደረገ በኋላ ተራፊውን ገንዘብ ለአስመጪው ይመልሳል።

ነገርን በምሣሌ ..... እንደሚባለው የያዝነውን ጭብጥ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ እንዲረዳን የሚከተለውን አስረጂ እንመለከት:: የተለያዩ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር አስገብቶ የሚሸጥ አንድ አስመጪ በዓመቱ መጨረሻ አንድ ሚሊዮን ብር አትርፏል እንበል ። አስመጪው ከዚህ ገቢው በመቶኛ 30 ብር የንግድ ትርፍ ግብር የመክፈል ግዴታ ተጥሎበታል። በዚህ መሠረት አስመጪው በዓመቱ መጨረሻ ለመንግሥት እንዲከፍል የሚጠበቀው ግብር 300 ሺ ብር ይሆናል ማለት ነው።

አስመጪው 300 ሺ ብር ግብር የሚከፈልበትን የንግድ ትርፍ ያገኘው በዚያ በጀት ዓመት /በ2002 ሊሆን ይችላል/ 25 የቤት መኪናዎችን ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቶ በመሸጥ ነው። አስመጪው እነዚህን ተሸከርካሪዎች በሚያስገባበት ወቅት በተለያዩ ጊዜ የንግድ ትርፍ ግብር ሲከፍል ቆይቷል። ይህ ክፍያ በዓመቱ መጨረሻ ሊከፈል ከሚገባው ግብር /300 ሺ ብር/ ላይ ታሳቢ የሚደረግ ነው።በዚህ መሠረት አስመጪው ተሸከርካሪዎችን ወደ ሀገር ሲያስገባ

የከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር መጠን ድምር 250 ሺ ብር ቢሆን በአስመጪው ያልተከፈለው የግብር መጠን 50 ሺ ብር ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ አስመጪው ልዩነቱን ለባለሥልጣኑ በመክፈል የሚፈለግበትን የግብር ክፍያ ያጠናቅቃል ማለት ነው። በተቃራኒው አስመጪው 25ቱን ተሸከርካሪዎች ወደ ሀገር ሲያስገባ የከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር መጠን 350 ሺ ብር ቢሆን አስመጪው የ50 ሺ ብር ግብር በትርፍነት ለባለሥልጣኑ ክፍሏል ማለት ነው። ስለዚህ ባለሥልጣኑ 50 ሺ ብር ለአስመጪው ተመላሽ ያደርጋል ማለት ነው። ባለሥልጣኑ ይህን የሚያደርገው አስመጪው ከማንኛውም ግብርና ቀረጥ ነፃ መሆኑን አረጋግጦ ነው።

5.1 ወደ ሃገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የሚሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር የማይመለከታቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እንደተሻሻለ አንቀጽ 52/5/ ላይ እንደተደነገገው ለንግድ የሚውሉ እቃዎች የሚለውን ሐረግ ትርጉም በመመሪያ እንዲወሰን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ድርጅቶችና ግለሰቦች ወደ ሃገር የሚያስገቡዋቸው እቃዎች ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ ተደርገዋል።

1. በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት በመንግስት መ/ቤት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የተካተቱ የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች፣
2. ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማህበራት /ክፍተህ ሚኒስትር ወይም ከሚመለከተው አካል የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲያቀርቡ/፣
3. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት የግል መገልገያ እቃዎቻቸውን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው ግለሰቦች፣
4. በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 2ኛ መደብ ከጉምሩክ እና ከሌሎች ቀረጦችና ታክሶች ነፃ ሆነው እንዲገቡ የተፈቀዱ እቃዎችን የሚያስመጡ ግለሰቦችና ድርጅቶች፣
5. በዲፕሎማቲክና ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ የሆኑ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ወይም ከንሱላር ሚሲዮኖች እና የእነዚሁ አባላት፣
6. በፌዴራል እና በክልል ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት /Tax Holiday/ የተሰጣቸው ግለሰቦች እና ድርጅቶች /ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርቡ/፣
7. የአምራችነት ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለሚያመርቷቸው እቃዎች በግብዓትነት የሚጠቀሙባቸው ጥሬ እቃዎች እና ለካፒታል እቃዎች የሚያገለግሉ መለዋወጫዎች በቀጥታ ለንግድ የማይውሉ በመሆኑ ከ3% የገቢ ግብር የቅድሚያ ክፍያ ነፃ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ባለ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሃገር ባስገቡት ጥሬ እቃ ሸቀጡን አምርተው ለገበያ በሚያውሉበት ጊዜ

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ስለማድረግ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት 2% ተቀናሽ የሚደረግባቸው ይሆናል፤

8. *ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ወይም ለማስፋፋት ወይም ለኃይል ማመንጫ ወይም የመገናኛ አገልግሎት ለመዘርጋት ወ.ዘ.ተ. ወደ ሃገር የሚገቡ የካፒታል እቃዎች /በቀጥታ ለንግድ የማይውሉ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት የካፒታል እቃዎች መሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከቀረበ/፤*
9. *የሰጦታ፣ የንግድ ማስታወቂያ እና የናሙና እቃዎች* /Sample Goods/ ፤
10. *በማዕድን እንዲሁም በፔትሮሊየም ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች /በልዩ ታክስ ህግ የሚተዳደሩ በመሆናቸው/፤*

6. ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባ በአንድ የቤት መኪና ላይ የሚጣለው ቀረጥና ታክስ እንዴት ይሰላል?

አንድ አስመጪ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋዋ 60,000 ብር የሆነ ባለ 1300 ሲ.ሲ የቤት መኪና ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቷል ብለን እናስብ። በመኪናው ላይ የሚጣለው ጠቅላላ ቀረጥና ታክስ እንዴት ሊሰላ ይችላል? ተከፋዩን ቀረጥና ታክስ በሁለት ዘዴዎች ለማስላት ይቻላል። በመጀመሪያው ዘዴ አስመጪው ሁለት ተግባራትን ያከናውናል። በቅድሚያ፣ የመኪናውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ያሰላል፤የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መኪናው የተገዛበት ዋጋ፣ ለኢንሹራንስ የተከፈለ ገንዘብ እና መኪናዋን ለማጓጓዝ የተከፈለው ገንዘብ ድምር ውጤት ነው። በመቀጠልም የመኪናዋን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (duty paying value) በመኪናዋ ጠቅላላ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ያባዛል። የብዜቱ ውጤት ተከፋዩ ቀረጥና ታክስ ይሆናል። በዚህ መሰረት የመኪናዋ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሆነው 60,000 ብር በመኪናዋ ጠቅላላ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ መጣኔ በ125% ሲባዛ ተከፋዩን ቀረጥና ታክስ 75,000 ብር እናገኛለን።

ጠቅላላ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ መጣኔ እንደመኪናዋ የፈረስ ጉልበት(ሲ.ሲ) ይለያያል። እስከ 1300 ሲ.ሲ ያላቸው መኪናዎች ጠቅላላ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ መጣኔ 125% ነው። *ከ1301 ሲ.ሲ እስከ 1800 ሲ.ሲ እና ከ1800 ሲ.ሲ በላይ ያላቸው መኪናዎች ጠቅላላ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ መጣኔ* በቅደም ተከተላቸው መሰረት 176.24% እና 244.55% ነው።

በሁለተኛው ዘዴ ተከፋዩ ቀረጥና ታክስ የሚሰላው በሚከተሉት ሰባት የስሌት ደረጃዎች ላይ ተመረኩዞ ነው።

ደረጃ አንድ

በዚህ የስሌት ደረጃ አስመጪ የመኪናውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ያሰላል።

ደረጃ ሁለት

በመቀጠልም አስመጪው ተከፋዩን የጉምሩክ ቀረጥ ያሰላል፡፡ ለምሣሌ የመኪናዋ የቀረጥ መስከፈያ ዋጋ 60,000.00 ብር ቢሆን ተከፋይ የጉምሩክ ቀረጥ 21 ሺ ብር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ተከፋዩ የጉምሩክ ቀረጥ የተሰላው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሆነውን 60ሺ ብር በመኪናዋ የቀረጥ ማስከፈያ መጣኔ በ35 በመቶ ተባዝቶ ነው፡፡

ደረጃ ሶስት

በዚህ ደረጃ ተከፋዩ ኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ አስመጪው የዕቃውን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ እና የጉምሩክ ቀረጥን ደምሮ በ30 ከመቶ ያባዛል (60000+21000) x30/100) ይህ ስሌት ተከፋዩን የኤክሳይዝ ታክስ /24 ሺ ብር/ ይሰጠናል፡፡

ደረጃ አራት

በዚህ ደረጃ አስመጪው ተከፋዩን የተጨማሪ እሴት ታክስ ያሰላል፡፡ ከዚህ ውጤት ላይ ለመድረስ አስመጪው የመኪናዋን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ፣ ተከፋዩን የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ ይደምራል፡፡ በመቀጠልም በተጨማ እሴት ታክስ መጣኔ ያባዛል(60000+21000+24000)x15/100 የዚህ ስሌት ውጤትም ተከፋዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ /15,795.00/ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ደረጃ አምስት

በዚህ ደረጃ አስመጪው ተከፋዩን ሱር ታክስ ያሰላል፡፡ ከትክክለኛው ስሌት ላይ ለመድረስ አስመጪው የመኪናዋን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ፣ ተከፋዩን የጉምሩክ ቀረጥ፣ ተከፋዩን ኤክሳይዝ ታክስ እና ተከፋዩን ተጨማሪ እሴት ታክስ በአንድነት ይደምራል፡፡ ድምሩ በ10 ከመቶ /በሱር ታክስ መጣኔ/ ሲባዛ ተከፋዩን ሱር ታክስ እናገኛለን፡፡ በዚህ መሠረት (60000+21000+24000+15795)x10/100=12,109.50 እናገኛለን፡፡ ወይም በዚህ ስሌት መሠረት ተከፋዩ ሱር ታክስ 12,109.5 ብር ይሆናል ማለት ነው፡፡

ደረጃ ስድስት

በዚህ ደረጃ ተከፋዩን ዊዝሆልዲንግ ታክስ እናሰላለን፡፡ ይህ ታክስ የሚሰላው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን በዊዝሆልዲንግ ታክስ መጣኔ በማባዛት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ተከፋዩ የዊዝሆልዲንግ ታክስ 60000x3/100=1800.00 ብር ይሆናል ማለት ነው፡፡

ደረጃ ሰባት

በዚህ ደረጃ ወደ ሀገር በገባችው የቤት መኪና ላይ የሚከፈለው ጠቅላላ ቀረጥና ታክስ ይሰላል፡፡ ታክሱ የሚሰላው አምስቱን የታክስ ዓይነቶች በመደመር ነው ወይም ቀደም ሲል ከደረጃ ሁለት ጀምሮ እስከ ስድስት የተሰሉትን ታክሶች በመደመር ነው፤ የጉምሩክ ቀረጥን፣ኤክሳይዝ ታክስን፣የተጨማሪ እሴት ታክስን፣ሱር ታክስን እና ዊዝሆልዲንግ ታክስን እንደምራለን፡፡ በዚህ መሠረት የተከፋዩ ቀረጥና ታክስ 21000+24300+15795+12109.5+1800=75000.50 ይሆናል፡፡ በዚህ ስሌት መሠረት ጠቅላላው ተከፋይ ቀረጥና ታክስ 75,000.50 ብር ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ ላይ የመኪናዋን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ስንደምር መኪናዋን ወደ ሀገር ለማስገባት አስመጪው ያወጣውን ጠቅላላ ገንዘብ 75,000.50+60,000=135,000.00 እናገኛለን ማለት ነው፡፡

በአበበ ሁናቸው